# Legacy International Spiritual Ministry
# 2019 GC Annual Summary Report



**Legacy International Spiritual Ministry**
**P.O.Box 192/1070**
**Cell # 251 930 651943**
**Act: #; Berhan Bank 2600010008458**
**Addis Ababa, Ethiopia**

*ለዉድ የሌጋሲ መንፈሳዊ አገልግሎት ደጋፊዎች!*

***ጉዳዩ፡ የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2019 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ***

ሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት የሶስተኛ ዓመቱን ጠቅላላ ጉባዔ የካቲት 1፣ 2012 (February 9፣ 2020) ባደረገበት ወቅት ሪፖርት እንደተደረገው፣ የተገኘዉን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የአገልግሎቱ አድማስ በአሜሪካ ትዉልደ ኢትዮጵያዉን አብያተ ክርስቲያናት መካከል ማስፋት መቻሉ ተገልጾኣል፡፡ በሀገር ዉስጥም ሆነ ከሀገር ዉጪ የዚህ ዓመት የእንቅስቃሴ ባብዛኛዉ በወለጆች ላይ ትኩረት እንደነበረዉም ለማወቅ ተችሏል፡፡

የአገልግሎቱ ቦርድ መልካም አመራር የሰጠ ሲሆን በበጀት ዓመቱ ዉስጥ እአአ የ2018 ማጠቃለያ ጠቅላላ ጉባዔ ዝግጅት ጨምሮ ሶስት መደበኛ ስብሰባዎችና ኦዲት በተመለከተ ሌላ አንድ ኢመደበኛ ስብሰባ አድርጓል፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች ቦርዱ በልዩ ልዩ አጀንዳዎች ላይ አመርቂ ውይይት በማድረግ ውሳኔዎችን በማስተላለፍ አቅጣጫ ሰጥቷል፡፡ ሌጋሲ ከሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎቶች ጋር በሀገር አቀፍ ኤግዚብሽን በ4ኛ ሩብ ዓመት (ኦክቶቤር) ተካፍሎኣል፣ ይህ ደግሞ አገልግሎቱን የበለጠ ለማስተዋወቅ ረድቷል፡፡

በዓመቱ በገቡት ቃል መሠረት፣ በጎ ፈቃደኞች፣ በጊዜያቸው፣ በዕውቀታቸውና በሀብታቸው ከአገልግሎቱ ጎን በመቆማቸዉ አመርቂ ሥራዎች ተሠርተዋል፣ ዉጤቶችም ታይተዋል፡፡ የእግዚአብሔር ጸጋ የበዛላቸዉ ይህን በደስታ አድርገዉታልና፡፡ በጥቅሉ የሌጋሲ አገልግሎት የበጎ ፈቃደኞች ዉጤት ነዉ ለማለት ይቻላል፡፡ በዕቅዱ መሠረት የአገልግሎቱ አንኳር ተግባር የሆነዉን ሥልጠና የመስጠት ሥራ ለሚመለከታቸዉ ተደራሾች በተለያዩ አካባቢዎች በመከናወኑ ባለፋት ዓመታት የተጀመረዉ አርአያነት እንዲቀጥል ሆኗል፡፡ በመሆኑም

## ክፍል አንድ - በግንባር የተሰጡ ሥልጠናዎች

### *ሀ. የወጣቶች አገልግሎት በተመለከተ*

**1ኛ** የልጆች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ መለኮት ኮርስ የማስተማር ሥራ ለመጀመሪያ ጊዜ እአአ ማርች 2017 መከናወኑ የሚታወስ ሲሆን፣ በተመሳሳይ በዚህ በጀት ዓመትም በሁለተኛዉ ሩብ **ለ20 ተማሪዎች** በሁለት ሳምንት ብሎክ ኮርስ ከኢትዮጵያ ሥነ መለኮት ኮሌጅ (ETC) ጋር በመተባባር ከኤፕሪል 15 - 25፣ 2019 በነበረዉ ጊዜ ተከናዉኗል፡፡

**2ኛ የግል ጊዜ ከጌታ ጋር** በተጠናከረ ሁኔታ መለማመድ እንድችሉ **በሰበታ ሙሉ ወንጌል ለ6 የወጣቶች** መሪዎች፣ **በቡታጅራ ሙሉ ወንጌል** ማርች 23፣ 2019 (መጋቢት 14፣ 2011) **ለ49 ወጣቶች** ፣ **በዲሲ (አሜሪካ) ኢመደባዊ** ማሰባሰብ በማድረግ የማተማርና ማሠልጠን ሥራ ተሠርቷል፡፡ በተጨማሪ በሰበታና በዲሲ አካባቢ ከወጣቶች ጋር በነበረዉ ግኑኙነት በሰባቱ የወጣቶች መንፈሳዊ ምሰሶዎች ላይ ትምህርትና ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

**የቅድመና ድህረ ሥልጠና ግብረ መልስ ትንተና በጥቅሉ** ከስልጠና በፊት ከ48 ግብረ መልስ ሰጪ ስልጠና ተካፋዮች መካከል 45%፣ የጥሞና ጊዜ የነበራቸዉ ቢሆንም ይህ ቁጥር ከስልጠናዉ በኋላ ወደ **71% ከፍ ብሎ ታይቶል፤** በመሆኑም ወዲያዉ የተደረገዉ እንቅስቃሴ **ዉጣት** (**Output)** እንደሚያሳየዉ **በልዩነት 26%** የሚሆኑ ሠልጣኞች በዚህ ልምምድ ዉስጥ ለመግባት እንደወሰኑና ቀድሞ ልምዱ የነበራቸዉም እንደሚቀጥሉ የሚያሳይ በመሆኑ የሚያበረታታ ነዉ፡፡



*ሀ. ኢቲሲ ተማሪዎች*

ኢየሱስ ጌታ ነዉ!!!



ለ. ኤግዚቢሽን ማዕከል ገለጻ

### ለ. የወላጆች አገልግሎት በተመለከተ

**1ኛ ከሰበታ ሙሉ ወንጌል** ጋር በመተባበር በሰበታ ከተማ ከፌብሩዋሪ 8-10, 2019 (የካቲት 1-3 ቀን 2011 ዓ.ም.) ለወላጆች በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝና በሰባቱ የወላጅነት ምሰሶዎች ላይ ሥልጠና ተስጥቷል፡፡ በዚህ ሥልጠና ላይ የተሳታፊ **ወላጆች** ቁጥር በከፍተኛዉ **29** ነበር፡፡

**2ኛ ከቡታጅራ ሙሉ ወንጌል** ጋር በመተባበር ከማርች 22-24፤ 2019 (ከመጋቢት 13-15 ቀን 2011 ዓ.ም) በሥልጠና ማዕከላቸዉ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝና በሰባቱ የወላጅነት ምሰሶዎች ላይ ለ99 **ወላጆች**ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡

**3ኛ ከደብረ ዘይት ለምለም መካነ የሱስ** ጋር በመተባበር ለ**75 ወላጆች** ሚያዝያ 23፣ 2011 (የአንድ ቀን) የወላጅነት (Parenting) ሥልጠና በግንባር ተሰጥቷል፡፡ ርዕሶቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጆች አያያዝ እና ሰባቱ የወላጆች መንፈሳዊ ምሰሶዎች ነበሩ፡፡


ሐ. ሰበታ ሙወ ወላጆች ሥልጠና


መ. ደብረዘይት ለምለም መካነ የሱስ ወላጆች ሥልጠና

**4ኛ በአሜሪካን ሀገር ከምትገኘዉ የስልቬርስፒሪንግ/ሜሪላንድ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር **ለ12 ወላጆች** (ጁን 1፣ 2019) በወላጅነት ላይ በግንባር ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ አጠቃላይ ርዕሱ ልጆች በክርስቲያን ቤተሰብ የሚል ሆኖ ሰባቱን መንፈሳዊ የወላጅነት ምሰሶዎች ላይ በማተኮር ነበር፡፡

**5ኛ በአሜሪካ ካሊፎርኒያ/ሳንዲያጎ ከምትገኘዉ ማራናታ ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር በግንባር የወላጅነት ሥልጠና **ለ24 ሰዎች** ተሰጥቷል (ጁን 29፣ 2019)፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጆች አያያዝ እና ልጆች በክርስቲያን ቤተሰብ በሚል ርዕስ በሁለት አሠልጣኞች ቀርቧል፡፡

**6ኛ በአሜሪካ ሜኔሶታ/ሚኒያፖሊስ ከምትገኘዉ ፓዎር ኦፍ ዘ ጎስፔል ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር በወላጅነት ላይ ሰፊ ትምህርት በእሁድ አምልኮ ላይ **በኦሮምኛ** ቋንቋ ተሰጥቷል፡፡ በግምት ወደ **40 ምዕመናን** የሚሆኑ ተካፍለዋል (ጁላይ 14፣ 2019)፡፡

**7ኛ በአሜሪካ ሜኔሶታ/ሚኒያፖሊስ ከምትገኘዉ ቤቴል ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር **ለ12** ወላጆች በግንባር የወላጅነት ሥልጠና ተሰጥቷል፡፡ ሥልጠናዉ የተሰጠዉ በፓዎር ፖይንት በመደገፍ **በኦሮምኛ ቋንቋ** ነበር፡፡


ሠ. ቡታጅራ ሙወ ወላጆች ሥልጠና

**ኢ የ ሱ ስ   ጌ ታ ነ ዉ!!!**



ረ. ናዝሬት ሙወ ቁ 2 ወላጆች ሥልጠና



ሰ1. ላፍቶ ፉሪ ሙወ ወላጆች ሥልጠና

### ለ. የወላጆች አገልግሎት በተመለከተ (የቀጠለ)

**8ኛ በኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መሪ መካነ የሱስ** ማኅበረ ምእመናን በእሁድ አምልኮ ላይ ነሐሴ 26፣ 2011 በሰባቱ ምሰሶዎች ላይ ያተኮረ ሰፊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝ ትምህርት ለምዕመናን ተሰጥቷል፡፡ በግምት ወደ **100** ምዕመናን ተካፍለዋል፡፡ **መሠዊያን ማደስ** በሚል ርዕስ ላይም ትምህርታዊ ስብከት በሌላ እሁድ (ጳጉሜ 3፣ 2011) ተደርጓል፡፡

**9ኛ ከናዝሬት ቁጥር 2 ሙሉ ወንጌል** ጋር በመተባበር የአንድ ቀን የወላጅነት ሥልጠና መስከረም 17፣ 2012 (Sept 27/2018) **ለ30 ወላጆች** ተሰጥቷል፡፡

**10ኛ ከላፍቶ ፉሪ ሙሉ ወንጌል ቤተ ክርስቲያን** ጋር በመተባበር ለሁለት እሁዶች (ከሰዓት ከሰዓት በኋላ) በከፍተኛዉ ቁጥር **ለ63 ወላጆች** የወላጅነት ሥልጠና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የልጅ አያያዝና በ7ቱ የወላጅነት ምሰሶዎች ላይ ***ታህሣሥ* 5 እና 12፣ 2012 ዓ.ም** ተሰጥቷል፡፡



ሰ2 . ላፍቶ ፉሪ ሙወ ወላጆች ሥልጠና

## ክፍል ሁለት - የአሠልጣኞች ሥልጠና

### የወላጆች አሠልጣኞች ሥልጠናና የማስተላለፍ ሥራ

ከአቃቂ/ቃሊቲ አካባቢ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጋር በመተባበር የወላጆች አሠልጣኞች ሥልጠና ከማርች 16 እና 17፣ 2011 ዓ.ም (መጋቢት 7 እና 8፣ 2011 ዓም) **ለ50 ሠልጣኞች** ተከናዉኗል፡፡ ተሳታፊዎች በህብረቱ አስተባባሪነት በአቃቂ ቃሊቲ አካባቢ ከሚገኙ የተለያዩ ወንጌላዉያን አብያተ ክርስቲያናት ነበሩ፡፡ እነርሱም ወንድማማች ቤ/ክ፣ የህይወት ብርሃን ቤ/ክ፣ ገነት ቤ/ክ፣ ሰላም ቃል ኪዳን ቤ/ክ፣ ገሪዝም ቤ/ክ፣ የሙሉ ወንጌል አጥቢያዎች፣ መሠረት ክርስቶስ ቤ/ክ፣ ማራናታ ቤ/ክ፣ ጉባዔ እግዚአብሔር፣ ወዘተ ነበሩ፡፡

**የሥልጠናዉ ይዘት እንደሚከተለዉ ነበር**፣ ሥልጠና የማሳለጥ አደራረግ፣ የልጆች ልማት፣ የልጆች አስተዳደግ እና አያያዝ፣ ሰባቱ የወላጆች መንፈሳዊ ምሰሶዎች ነበሩ፡፡ ወጪዉ ከአቃቂ ቃሊቲ ህብረት ጋር በመጋራት የተከናወነ ነዉ፡፡ ሥልጠናዉን የሰጡ ለልጆች ልብ ያላቸዉና ረዥም ልምድ ያካበቱ ሶስት ባለሞያዎችና የእግዚአብሔር ሰዎች ናቸዉ፡፡



ሸ . አቃቂ ቃሊቲ የወላጆች አሠልጣኞች ሥልጠና

**የሌጋሲ ዓለም አቀፍ መንፈሳዊ አገልግሎት እአአ 2019 ዓመታዊ ሪፖርት በአጭሩ**

**ኢ የ ሱ ስ  ጌ ታ ነ ዉ!!!**

**የወላጆች አሠልጣኞች ሥልጠናና የማስተላለፍ ሥራ (የቀጠለ)**

በተለያየ የሥልጠናዉ ይዘቶች ሠልጣኞች ወዲያዉኑ ያገኙትን ጥቅም (**Output)** ለማወቅ ግብረ መልስ ተሰብስቦ ነበር፡፡ ይህም የነበራቸዉን መሠረት በማድረግ ተጨማሪ ካገኙት ዕዉቀት አንጻር ሲተነተን ከፍተኛዉን የደረጃ ማሻሻል ያሳየዉ (አራት ደረጃ ማለት ነዉ) **ልጆችን በምሳሌነትና በሥርዓት በመቅጣት** በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆ **ስለ ማሳደግ** የተገኘዉ ዕውቀትና ግንዛቤ የተመለከተ ነዉ፤ ይህም **በጣም አነስተኛ** የነበረ ሲሆን **አራት ደረጃ** ወደ በቂ በላይ ከፍታ አሳይቷል፡፡ ይህ በወላጆች አካባቢ ይህ ፍላጎት በብዙ እንዳለና ትኩረት ተሰጥቶት ሊሠራ እንደሚገባ የሚያመለክት ነዉ፡፡

**የሁሉም ሥልጠናዎቹ ማጠቃለያ**

በአጠቃላይ በአሜሪካ ያሉትን ዲያስፖራ ጨምሮ በዓመቱ የተለያየ ግንባር ሥልጠናዎችና ትምህርት የተሳተፉ 566 ሰዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ 82 ወጣቶች እና 484 ወላጆች ይገኛሉ፡፡ በዓመቱ በአጠቃላይ **1192 ሰዎች** ሥልጠናና ትምህርት በ21 ጣቢያዎች (በሀገር ዉስጥና ዉጪ) የተካፈሉ ሲሆን ከዚህ ዉስጥ በወላጆች አሠልጣኞች ሥልጠና የሠለጠኑ 50 ሰዎች፣ በግንባር የሠለጠኑ 566 እና በተላለፈ ወላጆች አሰልጣኞች ስልጠና የሰለጠኑ 576 ወላጆችና ወጣቶች ይገኛሉ፡፡ የወጣቶቹ ቁጥርና ጣቢያ በኢቲሲ የተሰጠዉን ትምህርት ይጨምራል፡፡ ሆኖም በእንግድነት በኢቲሲ በክርስቲያናዊ ቤተሰብ እና ፊይዝ ዴቬሎፕመንት ላይ በተሰጡ ሌክቸሮች ላይ የተካፈሉትን አይጨመርም፡፡

የወላጆች አሠልጣኝ ሠልጣኞች (Cascading Down) በማስተላለፍ ረገድ በአቃቂ/ቃሊቲ ህብረትና በሌላ የሚገኙ የተለያዩ ዲኖሚኔሽን አጥቢያዎች መጠነኛ እንቅስቃሴ አድርገዋል፡፡ በመሆኑም በመጋቢት 2011 በተከናወነዉ የወላጅነት አሠልጣኞች ሥልጠና ላይ የተካፈሉ አጥቢያዎች ብዛት ወደ 20 የሚጠጉ ሲሆን 10 ከሚሆኑ ዲኖሚኔሽኖች የተዉጣጡ ናቸዉ፡፡ ከነዚህ ዉስጥ ወደ 14 የሚሆኑ አጥቢዎች የወሰዱትን ተግባራዊ ያደረጉ ሲሆን 6ቱ በስልክ ሪፖርታቸዉን ገልጸዋል፡፡ የተቀሩት ወይ ተግባራዊ ለማድረግ በእቅድ ይዘዋል ወይ ደግሞ አድራሻቸዉ አልገኘም፡፡

ከዚህ በታች ያለዉ መረጃ በስልክ የተሰበሰበ ነዉ፡፡ ሪፖርት ያጠቃለለዉ የሰርጢ ወንድማማች (25 ወላጆች፣ 6 ልጆች አገልጋዮች)፣ ሰላም ቃል ኪዳን (25 ወጣቶች፣ 400 ለሚሆኑ አምልኮ ጉባኤ ላይ)፣ ቱሉ ዲምቱ ጉባኤ እግ (ለ 4 ልጆች አገልጋዮች) ፣ ህይወት በር ክርስቶሰ (ለ20 ወጣቶች፣ ለ5 ልጆች አገልጋዮች) ፣ አቃቂ ሙሉ ወንጌል (ለ 11 ልጆች አገልጋዮች)፣ ሳሪስ ቃሊቲ ገነት ቤተ ክርስቲያን (ለ40 ወላጆች) ናቸዉ፡፡

**እአአ 2019 የሂሳብ እንቅስቃሴ**

እአአ 2019 (ጃኑዋሪ እስከ ዲሴምበር) ለዓመቱ ተይዞ የነበረው በጀት ብር 1049220 ሲሆን የተሰበሰበዉ ገቢ ብር 185,989.91 አጠቃላይ ወጪ ብር 138,259.84 ነበር፤ ካለፈዉ ዓመት የዞረዉ ከወጪ ቀሪ ብር 44,222.63 ታስቦና ወጪዉ ተሰልቶ፣ በ2019 መጨረሻ ላይ ወደሚቀጥለዉ ዓመት የዞረ ብር 91,952.70 መሆኑ በኦዲተር ተረጋግጦ ለጠቅላላ ጉባዔ ሪፖርት ተደርጎ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡

**እአአ ለ2020 ዓም ለአገልግሎቱ ብር 403,000.00 በጀት ጸድቋል፡፡**

**በመጨረሻም** አገልግሎቱ በእግሩ እንዲቆም በትጋት ለተንቀሳቀሱ፣ በራቸዉን በመክፈት በትብብር እየሠሩ ላሉ (አአ ዉስጥ፣ ከአአ ዉጭ) አብያተ ክርስቲያናት መሪዎችና ወጣቶች፣ ኤስ አይ ኤም ስብሰባ በሚኖረን ጊዜ ሁሉ ቦታ ስለፈቀደልን፣ የፌዴራል መንግሥት ፈቃድ ሰጥቶ መንቀሳቀስ እንዲቻል ስላደረገ፣ ጥልቅ ምስጋናና ዕዉቅና በዚህም ሪፖርት ይሰጣቸዋል፡፡

***እርስዎና ቤተሰብዎም ለዚህ አገልግሎት መሳካት የበኩሎዎን ድርሻ ስላበረከቱ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ፡፡***

**መጨረሻ**